



# አዲሲቷ ኔልሰን ማንዴላ

------ከግርማ ዳምጤ ሀብተየስ

ደህና አደርኩኝ ሌሊቱን ተመቻችቼ
በጥሩ አልጋዬ ላይ ተኝቼ
ማለፊያ ቁርስም ከበላሁ በኋላ
ከባለቤቴ ጋራ፣ እሄዳለሁ ወደ ስራ።
ምንም ሳላስብ ሳልቸገር
እየተነፈስሁ ነጻ አየር
እኖራለሁ ውጭ አገር።
አንቺ ግን ብርቱካን
በወህኒ ቤት ታስረሽ
በስቃይ በችግር ተከበሽ
ትኖሪያለሽ በአገርሽ።
ለአገር ለሕዝብ ሲባል
የከፈልሺው ዋጋ
የታገልሺው ትግል
ሆኖ አይቀርም ምናምን
ፍሬ ያፈራል አንድ ቀን።
አንቺም ትሆኛለሽ ለኢትዮጵያ
ለአፍሪካም ሁሉ በጠቅላላ
አዲሲቷ ኔልሰን ማንዴላ።

gdamte@puc.edu